# ዓባይ ደረቀ አሉ!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ዓባይ ደረቀ አሉ የወንዞች አባት፤
እጅግ ቢበዛበት የዜጎች ጩኸት፤
ዓባይ ደረቀ አሉ ድንጋዩ ፈጠጠ፤
ከሱ ጅረት ይልቅ የ'ንባ ጎርፍ በለጠ፤
ዳግም ላይታለብ ላይሰጥ ወተቱን፤
ጣናን አመከነ አሟጠጠ ምንጩን፤
እኔ ድርቅ ልበል እኔ ልሙትልሽ፤
ብሎ ዓባይ ደረቀ ጠቢያ ለልጆችሽ ::

ዓባይ ደረቀ አሉ ጣናን አሟጠጠ፤
ጦርነት ያማረው ቀረ እንደቋመጠ ::

በጭራሽ! እንዲያውም!
እንዲፈሰ አልሻም!
ንጹሕ የድሃ ደም፤
በኔ ተመካኝቶ፤
መከበር መኮፈስ አይገኝም ከቶ፤
ብሎ ዓባይ ደረቀ፤
ጦር ለናፈቃቸው ቁርጡን አሳወቀ ::

ዓባይ እንደ እንቶኔ ጩካኝ ዜጋ አይደለም፤
በሱ ጅረት ፋንታ ንጹሕ ደም አይፈሰም ::
« ዓባይ ሞላልሽ! ሞላልሽ!
አዘቅት ሆነልሽ! »
ብሎ ያዜመለት፤
ሸማግሌው ወጣት፤
ኮረዳዋ አሮጊት፤
ሳይቀሩ ሕፃናት፤
እንዴት?! ለምን?! ይሙት፤
እንቶኔ ሊሞካሽ ሊዘባነንበት ::

*አገር አመሳቅሎ አገር ወዳድ መሳይ፤*
*ያፍ ዝልዝል ለማቅረብ ዛሬ መሚል ባባይ፤*
*ያውቀዋል ልባችን ይቅር መዘላበድ፤*
*አይገኝምና ካባይ ወዲያ ዘመድ።*

*የማይሞት ወንዝ ሞተ ዓባይ ደረቀ አሉ፤*
*በፈለቀበት ምድር በዝቶበት በደሉ፤*
*ዳግም ሳይታለብ ሳይሰጥ ወተቱን፤*
*ጣናን አመከነ አሟጠጠ ምንጩን፤*
*እኔ ድርቅ ልበል እኔ ልሙትልሽ፤*
*ብሎ ዓባይ ደረቀ ጦቢያ ለልጆችሽ።*

*አንተስ ?! እኔስ ?! አንቺስ ?! እኛስ ?!*

*አንድ ቀን፡*
*ለዓባይ ወንዝ መታሰቢያ ትሁንልኝ።*